# የድነት ትምህርት

አዘጋጅ

የሕይወት እንጀራ አገልግሎት

(2002 ዓ.ም.)

**ቢጋር**

**ርዕስ**

***መግቢያ:- የዘላለም ሕይወት እንዳልዎት እርግጠኛ ነዎት?***

**ትምህርት 1** የዘላለም ሕይወታችን

**ትምህርት 2** የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ

**ትምህርት 3** ኃጢአትና መዘዙ

**ትምህርት 4** የእግዚአብሔር መፍትሄ

**ትምህርት 5** ክርስቶስ ቅጣታችንን ተቀብሎልናል

**ትምህርት 6** የእግዚአብሔር ልጁን በእኛ ፈንታ የመተካት መርህ

**ትምህርት 7** የእግዚአብሔር ልጅ መሆን

**ትምህርት 8** ለመዳን፣ የእኔ ድርሻ ምንድን ነው?

**ትምህርት 9** ንስሃ

**ትምህርት 10** የመልካም ተግባራት ፋይዳ ምንድን ነው?

***ማጠቃለያ***



## መግቢያ

## የዘላለም ሕይወት እንዳልዎት እርግጠኛ ነዎት?

በመጀመሪያ እንኳን ወደዚህ የድነት ትምህረት ጥናት መጡ እያልን መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ላደረጉት ቆራጥ ውሳኔ ልናደንቅዎ እንወዳለን። ይህ ‹የድነት ትምህርት› ኮርስ የዘላለም ሕወትዎን በተመለከተ ወሰኝ ርእሰ ጉዳይ መሆኑን ልብ ይበሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እርሶ ወደ መንግስተ ሰማይ ለሚያደርጉት የጉዞ መሰናዶ በእጅጉ እንደሚጠቅሞዎት እናምናለን። በዚህ ኮርስ ውስጥ የቀረቡ ሃሳቦች የእኛን አስተሳሰብና ግምት የያዙ ሳይሆኑ በቀጥታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን የሚናገሩ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሱ ሲናገር ልንናገር፣ ዝም ሲል ደግሞ ዝም ልንል ግድ ነውና። የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ልናደርጋቸው፣ በጽሐፉ በስማቸው የሚጠራቸውንም በግልጽ ልንጠራቸው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የነሰ፣ የበዛ፣ ወይም የተለየ ነገር ሁሉ የስህተት ትንህርት ነው።

ከእግዚአብሔር ቃል እውቀት ማነስ የተነሳ በተፈጠሩት በርካታ ሃይማኖቶች ምክኒያት በአለም ሕዝቦች መካከል ከፍተኛ ግራ በጋባት ይስተዋላል። በአሁኑ ሰአት በአለማችን ላይ የተለያየ አስተምህሮዎች፣ የስነ መለኮት ምልከታዎች እና አስተሳሰቦች ያልዋቸው ከ 600 በላይ ቤተ እምነቶች ይገኛሉ። በእነዚህ በርካታ እምነቶች ‹የእመን› ጥያቄ የሚቀርብላቸው የአለማችን ሰዎች ምን እና ማንን ማመን እንዳለባቸው ለመወሰን ግራ ተጋብተዋል። አዳኛችን የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈቃዱ በከፈለው ስቃይና ሞት ለኃጢአታችን ይቅርታ የሚያስፈልገውን ሁሉ አቅርቦልናል። በፍርድ ቀን ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር ወደ ወደ ዘላለም እቶን እሳት መጣል አይገባንም። እናም ለመዳን የወንጌልን እውነት መታዘዝ ይኖርብናል። ወንጌል ምንድን ነው? ለመዳን ምን ማድረግ ይኖርብኛል? በዚህ ጥናት ውስጥ እግዚአብሔር በሰማይ ያዘጋጀልንን የዘላለም ሕይወት ስጦታ ለመውረስ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብን የሚናገረውን አብረን እናያለን።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ጥቅሶች በሙሉ *ጠመም/ዘመም* ባለ የፊደል አጻጻፍና **ደማቅ** *ሆነው የቀረቡ ሲሆን* ለእነዚህ ጥቅሶች ልብዎንና አእምሮዎን ሊከፍቱ ይገባል። እግዚአብሔር በእነዚህ *ቃሎች* ውስጥ ምን ሊያስተላልፍ እንደፈለገ *መግለጥ* የዚህ ኮርስ ዋነኛ *አላማ* ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱትን እነዚህን ጥቅሶችን ሲያነቡ <u>ለተሰመረባቸው</u> *ቃላት* ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ እናሳስባለን።

"የዘላለም ሕይወት እንዳልዎት እርግጠኛ *ነዎት*?" የሚለው ይህ ኮርስ በ10 ትምህርቶች የተከፋፈለ ነው። ከእያንዳንዱ ትምህርት በኋላ የምርጫ እና የእውነት/ውሸት ጥያቄዎች ቀርበዋል። የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ከጥያቄዎቹ *ጋር* በቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ያገኙዋቸዋል። ይህን ኮርስ ማጥናት በዘላለም ሕይወትዎ ላይ *ታላቅ* ሚና እንዲጫወት የዘወትር ጸሎታችን ነው። ማነኛውም ጥያቄ ሆነ አስተያየት ቢኖርዎ ለመምህሮ ያሳውቁ ወይም በሚከተለው አድራሻ ቢልኩልን ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት *ቃል* እንገባለን።



## ትምህርት 1

## የዘላለም ሕይወታችን

***የዘላለም ሕይወት ስለማግኘትዎ እርግጠኛ ነዎት?*** ይህ ጥያቄ የዘላለም ሕይወትዎን በተመለከተ ዋነኛ ጥያቄዎ መሆን አለበት። ዛሬ ቢሞቱ በእርግጠኝነት በቀጥታ ወደ ገነት እንደሚሄዱ ያውቃሉ? ነፍስዎ ከስጋዎ ከተለየች በኋል ይህን የምርጫ እድል ዳግመኛ የማያገኙት በመሆኑ ጥያቄውን በቸልታ ሊያልፉት አይገባም። አንድ ቀን ለዚህ ጥያቄ የሰጠነውን ምላሽ ለማወቅ ሁላችን በፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን። የሰው ልጅ ሊያስቀራቸው የማይችላቸው ሁለት ነገሮች ከፊቱ ይጠብቁታል። እነዚህ ነገሮች ሞትና ፍርድ ይሰኛሉ። ***‹‹ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፤››*** ዕብራዊያን 9፡27። ማንም ሰው እነዚህን ነገሮች ሊያመልጥ አይችልም።

ማንም ሰው ስለነገው ቀርቶ ከጥቂት ሰኮንዶች በኋል ስለሚሆነው ነገር እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በምንም መንገድ ይህን ጥያቄ ለነገ ልንገፋው አንችልም። እግዚአብሔር በያዕቆብ መልእክት 4፡14 ላይ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል፦ ***‹‹…ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና።››***

ለእኛ አእምሮ ‹‹ትክክል›› እና ‹‹ስህተት›› በሚመስሉን መመዘኛዎች ላይ ተመስርተን የዘላለም ሕይወትን የሚያህል ውድ ነገር ላይ ስህተት መስራት የለብንም። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በስሜቶቻችንም ላይ ቢሆን መመስረት የለብንም። እስቲ መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ 14፡12 ላይ የሚለውን እንመልከት፦ ***‹‹ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው››***። ለውሳኔዎቻችን ትክክለኛነት ማረጋገጫው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆን ይገባዋል።

ደኅንነትዎን በተመለከተ የግልዎ ግምቶች ምንድን ናቸው? ብዙዎቹ እኛና ሰዎች የምናቀርባቸው ግምቶች እግዚአብሔር በቃሉ ካስቀመጠው እውነታ ጋር የሚቃረኑ ናቸው። ስለዚህ ያሉንን ግምቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል መፈተሽ ይኖርብናል። ይህንን በምናደርግበት ወቅት በእኛና በእግዚአብሔር ቃል መካከል

ያሉ በርካታ ልዩነቶችን ማስተዋል እንጀምራለን። ጌታችን በማርቆስ 7፡7 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ በእውነት ትንቢት ተናገረ››።*** አምልኮአችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሰረተ ሲሆን ከንቱ ይሆናል። የእነዚህ ሁሉ አደናጋሪ ትምህርቶች ምንጭ እግዚአብሔር ይመስሎታል? ፈጽሞ! 1ቆሮንቶስ 14፡33 እንዲህ ይላል፡- ‹‹***እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው***››። ሐዋሪያው ጴጥሮስ ለአይሁድ ሸንጎ በሐዋሪያት ሥራ 5፡29 ላይ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- ***‹‹ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል››።*** በመጨረሻው ዘመን ሰውም ሆነ የእኛ አስተያየት ከፍርድ ለማምለጥ ምክኒያት አይሆኑንንም። ከፍርድ የሚያስመልጠን በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ያመነው ቁምነገር ብቻ ነው። ጌታ ኢየሱስ፣ ደኅንነትን (ትምህርተ ድኅነን) አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በነገረን መሠረት ብቻ የምንዳኝበት የፍርድ ቀን ይመጣል። ፍርድ የሚሰጠው በዚህ መመዘኛ ብቻ ነው፤ ምክኒያቱም ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሯልና፣ የዮሐንስ ወንጌል 12፡48 ***‹‹የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል››።*** ስለዚህ ደኅንነቶን አስመልክቶ ማንም ሰው (እኛን ጨምሮ) የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በሌለበት የግሉን አስተያየት ቢሰጥዎ ሊቃወሙት ይገባል። ከነፍስዎ በላይ ምን ሊያሳስቦት የሚችል ነገር ይኖራል?

የነፍስዎን ዋጋ በአለም ያለ ምንም ነገር ሊመጥነው እንደማይችል ያውቃሉ? ማቴዎስ 16፡26 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?››*** ነፍሳችን ዘላለማዊ ናት። እናም ይህችን ነፍስ ለዘላለም በእቶን እሳት ውስጥ እንድትኖር ሊያደርጋት የሚችሉ ጉዳዮችን ሁሉ በቸልታ መመልከት ፈጽሞ አይገባንም።

---

## የትምህርት 1 ጥያቄዎች

## የዘላለም ሕይወታችን

1) ስለደኅንነት ያለን እውቀት የተሳሳተ ቢሆን የቅጣት ፍረድ የጠብቀናል?

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

2) (ምሳሌ 14፡12) ለሰው መልካም የምትመስል መንገድ ፍጻሜዋ ምንድ ነው?

ሀ) ዘላለማዊ ሕይወት

ለ) መንፈሳዊ ሞት

ሐ) ስኬት

3) ደኅንነታችንን በተመለከተ በስሜቶቻችን ላይ መደገፍ አዋጭ መፍትሔ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

4) (ማርቆስ 7፡7) የሰውን ስርአት የሆነ ትምህርት መከተል፡-

ሀ) ከንቱነት ነው

ለ) ችግር የለውም

ሐ) እግዚአብሔርን አያስከፋውም

5) (ዮሐንስ ወንጌል 12፡48) በፍርድ ቀን፣ ለፍርድ የሚውለው መመዘኛ ምንድ ነው?

ሀ) እውቀታችን

ለ) የክርስቶስ ቃል

ሐ) የሰበኩን ሰዎች ቃል

6) (ዕብራዊያን 9፡27) በሕይወት ዘመናችን የማናመልጣቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

1. _______________

2. _______________

## ትምህርት ሁለት

## የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ

ሁሉን የሚያውቅ አምላካችን ክርስቶስ በፍረድ ቀን ብዙዎች እንደሚጠፉና ጥቂቶች ብቻ እንደሚድኑ አስረግጦ ነግሮናል። ማቴዎስ 7፡13-14 እንዲህ ይላል፦ ***‹‹በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፣ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው››***። ይህ ጉዳይ ትኩረታችንን ሊስብ የሚገባ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት በርካቶቹ የአለማችን ሕዝቦች መንግስተ ሰማይን አይወርሱም። እነዚህ ሰዎች በሰፊው ጎዳና ወደዘላለም ጥፋት የሚነጉዱ ናቸው። ይህንን ማስጠንቀቂያ ያለማመቻመች ልንቀበለው ይገባል። ጌታ ኢየሱስ እንዳለው የሚድኑት ጥቂቶች ናቸው።

ለመሆኑ ጥቂት ሲባል ምን ያህል ነው? በ 1ጴጥሮስ 3፡20 ላይ እንዲህ ተጽፏል፦ ***‹‹ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም››።*** በኖኅ ዘመን ምድራችን ላይ እስከ ሁለት መቶ ሚሊዮን ሰዎች ይኖሩ እንደነበር ይገነታል። ነገር ግን ከእነዚህ ሰዎች መካከል ከጥፋት ውሃ መትረፍ የቻሉት ስምንት ሰዎች ብቻ ነበሩ።ይህ አስደሳች ቁጥር አይደለም። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በ 2ጴጥሮስ 3፡9 ላይ ***‹‹ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል››*** ቢልም፣ ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡13-14 ላይ ስለዘላለም ሕይወት ሲናገር ደኅንነት የሚያገኙት ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ ይናገራል ***‹‹በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው››።*** የተቀሩት በርካታዎቹ፣ የዘላለም ሕይወታቸውን እሳቱ በማይጠፋበት ገሀነም ያጠፋሉ።

ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያደርሱ ሁለት መንገዶች አሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ብቻ ወደ መንግስተ ሰማይ ያደርሰናል። የሰው ልጅ በአሁኑ ሰአት ከሁለት በአንዱ መንገድ ላይ ይገኛል። እርሶ በየትኛው መንገድ ላይ እንዳሉ ያውቃሉ? ምርጫው የእርሶ ነው። ነጻ ፈቃድ አሎት። ከእንስሳ ከሚለይዎት ነገሮች መካከል አንዱ ይህ ነጻ ፈቃድዎ ነው።

እግዚአብሔር ማንም እንዳይጠፋ የሚፈልግ ቢሆንም፣ ምርጫውን ግን ለእኛ ሰጥቷል። 2ጴጥሮስ 3፡9 እንዲህ ይላል፦ ***‹‹ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ***

***ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል››።*** 1ጢሞቴዎስ 2፡4 ስለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው››።*** እንግዳው ለመዳን በእጃችን ላይ ያለውን ውሳኔ እንጠቀም።

ደኅንነትን ለማግኘት ስለ ደኅንነት ትክክለኛ እውቀት ሊኖረን ይገባል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- ***‹‹እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው››*** የዮሐንስ ወንጌል 8፡32። ለመሆኑ አርነት የሚያወጣን እውነት ምንድን ነው? በዮሐንስ ወንጌል 17፡17 ላይ እንዲህ የሚል ቃል ሰፍሮ እናገኛለን፡- ***‹‹በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው››።*** ስለዚህ ወደ መንግስተ ሰማይ እንድንገባ አርነት የሚያወጣን እውነት ያለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው።

---

## የትምህርት ሁለት ጥያቄዎች

## የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ

1) (ማቴዎስ 7፡13-14) ምን ያህል ሰዎች ወደመንግስተ ሰማይ ይሄዳሉ?

ሀ) በርካቶች

ለ) ጥቂቶች

ሐ) ሁሉም

2) (2ጴጥሮስ 3፡9) እግዚአብሔር ሁሉም ___________ አይፈልግም።

ሀ) እንዲጠፉ

ለ) እንዲድን

ሐ) ንስሃ እንዲገባ

3) በ (1ጢሞቴዎስ) መሰረት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምንድን ነው?

ሀ) ሁሉም ሰው እንዲዝናና

ለ) ሁሉም ሰው እንዲድን

ሐ) ሁሉም ሰው እንዲጠፉ

4) (ዮሐንስ 8፥32) አርነት (ነጻ) የሚያወጣን ምንድን ነው?

ሀ) ገንዘብ

ለ) የሃይማኖት ስም

ሐ) እውነት

5) እውነት ምንድን ነው?

ሀ) እውቀታችን

ለ) የእግዚአብሔር ቃል

ሐ) የሰባኪዎቻችን ቃል

8) ነጻ የሚያወጣን ብቸኛ ነገር የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት



## ትምህርት 3

### ኃጢአትና መዘዙ

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለይቶናል። ኢሳይያስ 59፡2፣ ***‹‹ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል››።*** ከእግዚአብሔር የለየን ኃጢአት ነው። ሮሜ 3፡23 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል››።*** በዚህ ምድር ላይ ከኖረ ሰው ኃጢአት ያልሰራ ጌታችን ኢየሱስ ብቻ ነው። ስለዚህ ሁላችን ደኅንነት ያስፈልገናል። 1ዮሐንስ 1፡8 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም››።*** ሰው እራሱን በማሳት የኃጢአት ችግር የለብኝም ሊል ይችላል። ይህንን ሲል ግን ምን እያለ እንደሆነ 1ዮሐንስ 1፡10 ያሳየናል፡- ***‹‹ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም››***። እግዚአብሔር፡- ሁሉ ኃጢአት ሰርተዋል ሲል ሁሉም ሰርተዋል ማለት ነው።

ሮሜ 6፡23 የኃጢአት መዘዝዋ ምን እንደሆነ ይነግረናል፡- ***‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው››***። ሞት መለየት ማለት ነው። በአካል ስንሞት አካላችን በመቃብር ጉድጓድ ውስጥ ሲቀር ነፍሳችን ግን ወደሰራት አምላክ ትሄዳለች። የመክብብ መጽሐፍ 12፡7 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ››።*** በአካላዊ ሞት ነፍስ ከስጋ ትለያለች።

በሮሜ 6፡23 ላይ ***‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው››።*** እንደሚል አይተናል። ይህ ሞት ግን መንፈሳዊ ሞት ነው። ይህም ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው። ከእግዚአብሔር የተለዩቱ ደግሞ አድራሻቸው ገሃነም ይባላል፣ ራዕይ 21፡8፡- ***‹‹ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው››***። ይህ ሁለተኛ ሞት ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር ማለት ነው።

## የትምህርት 3 ጥያቄዎች

## ኃጢአትና መዘዙ

1) (ኢሳይስ 59፡2) እኛን ከእግዚአብሔር የለየው ምንድን ነው?

ሀ) ትልቅ ገደል

ለ) መልካምነታችን

ሐ) በደልና ኃጢአታችን

2) (1ዮሐንስ 1፡8) ኃጢአት የለብንም ብንል

ሀ) ስህተተኞች ነን

ለ) ትክክለኞች ነን

3) (ሮሜ 3፡23) ምን ያህሉ ሰው ኃጢአትን ሰርቷል?

ሀ) ጥቂቱ

ለ) በርካቶቹ

ሐ) ሁሉም

4) (መክብብ 12፡7) በአካል ስንሞት

ሀ) ነፍሰችን ከስጋ ትለያለች

ለ) ነፍሳችንና ሥጋችን ወደመቃብር ይሄዳሉ

ሐ) ነፍሳችንም ሆነ ሥጋችን ወደ አለመኖር ይሸጋራሉ

5) ከእግዚአብሔር መለየት ማለት መንፈሳዊ ሞት ማለት ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

6) (ራዕይ 21፡8) ሁለተኛው ሞት ማለት

ሀ) በአካል መሞት

ለ) ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር

ሐ) በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ውስጥ ለዘላለም መኖር

## ትምህርት 4

## የእግዚአብሔር መፍትሔ

ለሰው የኃጢአት ችግር እግዚአብሔር መፍትሄ አዘጋጅቷል። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው። ዮሐንስ 3፡16፣ ***‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና››።*** ለፍስን ለሌላው አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ምን ሊሆን ይችላል?

እግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ሳይሆን ጻድቅ ፈራጅም ነው። ዮሐንስ 5፡30፣ ***‹‹እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፣ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና››።*** ፍትህ በኃጥኡ ላይ ይፈርዳል። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡- ባንክ ስዘርፍ ተገኝቼ ለፍርድ ወዳጄ የሆነ ዳኛ ፊት ቀረብኩ እንበል። ይህ ዳኛ ወደእርሱ ከጠራኝ በኋላ የክስ ወረቀትህን እቀደዋለሁ፤ ከአሁን ጀምሮ ከፍርድ ነጻ ነህ፤ ውጣ፤ ቢለኝ፣ ጻድቅ ፈራጅ ያሰኘዋል? ፈጽሞ! እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው።

እግዚአብሔር ሕግ ሰጠ፣ የሰው ልጅ ተላለፈው፣ ፈጣሪም የጽድቅ ፍርድ አስተላለፈ። ይህም ፍርድ **<u>ሞት</u>** ይባላል። የሰው ልጅ በሞት ፍርሃት ውስጥ እየማቀቀ ለበርካታ አመታት በምድር ላይ የስቃይ ኑሮ መግፋት ጀመረ።

ይህን ፍርድ ያስተላለፈው አምላክ ጻድቅ ብቻ ሳይሆን የፍቅር አምላክ በመሆኑ፣ ከእስትንፋሱ የተካፈለው ሰው በምድር ላይ ሲሰቃይ ማየት አላስቻለውም። በዚህም ምክኒያት ጻድቅ ፈራጅነቱንና የፍቅር አምላክነቱን አዋህዶ የሚያሳይ **<u>ሌላ</u> <u>የድነት</u> <u>መንገድ</u>** ለሰው ልጅ አዘጋጀ፤ ይህ የድነት መንገድ ጽንፍ የሚመስሉትን የአምላክ ሁለት ባሕሪያት (ፍርድና ምሕረት) በአንድ መስመር ያገናኘ አስገራሚ ክስተት ነበር። እግዚአብሔር በሰው ዘር ሁሉ ላይ ያሳለፈው ሊታጠፍ የማይችል **<u>የሞት</u> <u>ፍርድ</u>** ሳይቀለበስ የሰው ልጅ ከተቆጣው አምላኩ ጋር ታረቀ። የአገራችን የእምነት ሊቃውንት ይህንን ሁኔታ ግሩም በሆነ መንገድ እንዲህ በማለት ይገልጹታል። «እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ያዳነበት ጥበቡ ተጠበበች።´ የዚህ አስገራሚ ትእይንት ጀማሪና ፈጻሚው ደግሞ ምንም በደል ያልተገኘበት ኢየሱስ ነበር። እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ የተቆጣውን ቁጣ በኢየሱስ ላይ አሳረፈው፤ ፍርዱን አሳየ። ኢየሱስ ስለ ኃጢአተኞቹ ስለ እኛ **<u>ሞተ</u>**። በእርሱም ምክኒያት

የሰው ልጅ ምኅረትን ተቀበለ። ከፈጣሪውም የፍርድ ቁጣ ተረፈ ***‹‹ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን››*** **(ሮሜ. 5፡9)**።

እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ብቻ ሳይሆን የበቀል አምላክም ጭምር ነው። ዕብራዊያን 10፡30-31 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና፤ ደግሞም። ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው››።*** ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን በፍቅር አምላክነቱ ብቻ ማወቅ ይሻሉ። ይህ ግን ስህት ነው። በፍርድ ቀን ሁሉ ሰው በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ እንዴት ያለ አስፈሪ ነገር እንደሆነ ያውቃሉ።

ኢየሱስ መሞት ለምን አስፈለገው? ምክኒያቱም እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ብቻ ሳይሆን ጻድቅ ፈራጅም ጭምር ስለሆነ፡ ፍትህ ከፍረድ ውጪ ሊታሰብ አይችልም። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የኃጥኡን ኃጢአት እነዴት እነደሚያነጻ ገልጹዋል። ለኃጢአታችን መንጻት ይህንን መንገድ ልንከተል ይገባል። ኩነኔ ያለባቸው ሁሉ ይህን የእግዚአብሔር መንገድ ያልተከተሉቱ ናቸው። እነዚህም ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሚሆንባቸውን 2ተሰሎንቁ 1፡8-10 እንዱህ በማለት ይገልጽልናል፡- ***‹‹እግዚአብሔርን የማያውቁትን፣ ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር፣ ምስክርነታችንንም አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፥ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ››።***

እግዚአብሔር የጸጋ አምላክም ጭምር ነው። ጸጋ ለማይገባቸው ሰዎች የተሰጠች የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነች። ሮሜ 3፡23-24 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል››።*** ሁላችን ኃጢአትን አድርገናል። በዚህም ምክኒያት ሁላችን የገሃነም ፍርድ ይገባናል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በማይገባን ስጦታ (በጸጋ) ማለትም በክርስቶስ ቤዛነት እኛን ሊያድን ወደደ። ቤዛነታችን ክርስቶስ ነው።

ሰው የሚድነው በጸጋው ነው። በኤፌሶን 2፡8-9 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- ***‹‹ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም››።*** ‹‹በእምነት መታዘዝ›› (ሮሜ 16፡26) በኩል በጸጋ እንድናለን። ማንም በመልካምነቱ ወደ መንግስተ ሰማይ የመግባት ድፍረት የለውም፤ ምክኒያቱም ሁሉ ኃጢአትን አድርገዋልና። በጎነታችን ደጎነታችንን

አይገዛልንም። መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 17፡10 ላይ እንዲህ ብሎናል፦ ***‹‹እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ። የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ››።*** ደኅንነታችንን ለማግኘት የሚያስችል ፍጹም ሥራ ልንሰራ አንችልም። ኢሳይያስ 64፡6 ይመልከቱ፦ ***‹‹ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል››።*** በማናችንም ውስጥ ለመዳን የሚሆን ምክኒያት አልተገኘብንም። ሁላችንን የሚያድነን የተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

---

## የትምህርት 4 ጥያቄዎች

## የእግዚአብሔር መፍትሄ

1) (ዮሐንስ 3፡16) እግዚአብሔር አለሙን ሁሉ ስለወደደ

ሀ) በማንም ላይ አይፈርድም

ለ) ልጁን በእኛ ምትክ እንዲሞት ሰጠ

ሐ) ሁሉም ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገባ ፈቀደ

2) ከኃጢአታቸው የሚሞቱትን እግዚአብሔር ይቀጣል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

3) (ዕብራዊያን 10፡31) በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ

ሀ) የሚያስፈራ ነው

ለ) የሚያስደስት ነው

ሐ) መልካም ነገር ነው

4) ፍትህ ኃጥኡ ላይ ይፈርዳል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

5) (ሮሜ 3፡23-24) ሁላችን ኃጥአን ስለሆንን

ሀ) እግዚአብሔር ስለኃጢአታችን አይፈርድብንም

ለ) ሁሉም የጠፋል

ሐ) በክርስቶስ በኩል በሆነው ቤዛነት ሰዎች ይጸድቃሉ

6) ያለ አንዳች ልዩነት የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአትን አድርገዋል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

7) (ኤፌሶን 2፡9-9) የምንድነው

ሀ) እንዲያው በእግዚአብሔር ጸጋ

ለ) በመልካም ሥራችን

ሐ) ኃጢአት ላለማድረግ በምናሳየው ጥረት

8) (ሉቃስ 17፡10) የታዘዝነውን ሁሉ ካደረግን በኋላ

ሀ) የማንጠቅን ባሪያዎች ነን

ለ) ወደ መንግሰተ ሰማይ ለመግባት ብቃት እናገኛለን

ሐ) የእግዚአብሔር ጸጋ አያስፈልገንም

9) (ኢሳይያስ 64፡6) ጽድቃችን

ሀ) እግዚአብሔር እንዲያድነን ያስገድደዋል

ለ) የሚያስደንቅ ነው

ሐ) እንደመርገም ጨርቅ ነው

10) የሚያድነን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት



## ትምህርት 5

## ክርስቶስ ቅጣታችንን ተቀብሎልናል

ሁላችን ኃጢአትን አድርገናል። እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ እንዲሆን ደግሞ ለኃጢአታችን የሚገባንን ፍርድ ልንቀበል ይገባናል። ይህም ደሞዝ ሞት ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ይህንን ቅጣት በእኛ ፈንታ ተቀብሎልናል። ሮሜ 5፡6-10 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና››***። ይህን ፍቅር ለመረዳት አዳጋች ነው።

በተጨማሪ 1ጴጥሮስ 3፡18 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ››***። ዳግመኛ ወደ እግዚአብሔር እቅፍ እንድንመለስ ጻድቅ የሆነው ክርስቶስ ኃጥኣን በሆነው በእኛ ፈንታ መሰቃየት ነበረበት። ***‹‹እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው››*** (2ቆሮንቶስ 5፡21)። ክርስቶስ እኛ ፈጽሞ ልንሰራው የማንችለውን ሥራ ሰርቶልናል። እዳችንን ከፍሎልናል። የሰው ልጅ ይህንን እዳ መክፈል ቢችል ኖሮ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ባላስፈለገው ነበር። በበደላችን ሙታን ነበርን፣ ነገር ግን ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ክርስቶስ በእኛ ፈንታ እንዲሞት በማድረግ የጽድቅ ፍርዱ ሳይዛባ ከሞት አዳነን።

ሰው የሚድንበት ብቸኛ መንገድ ክርስቶስ ብቻ ነው። ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። ዮሐንስ 14፡6 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም››።*** ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት መንገድ ክርስቶስ ነው። በተጨማሪ የሐዋሪያት ሥራ 4፡12 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና››።*** በሙሐመድ፣ በቡድሃ፣ በአይሁድነት፣ ወይም በሌሎች በማናቸውም የሃይማኖት ስሞች መዳን የለም። እኛ በፈጠርነው የክርስትና ሃይማኖት ስርአቶችም ጭምር መዳን የለም። ደኅንነታችን እዳችንን በከፈለው በክርስቶስ ብቻ ነው።

እዳችንን ለመክፈል ክርስቶስ ተሰቃይቷል። የተቀበለውን መከራ ማሰብ አእምሮችን ፈጽሞ አይችልም። ክርስቶስ ወደዚህ አልም የመጣው በሞቱ እዳችንን ለመክፈል ነው። የክርስቶስን ሞት የሚተነብዩ በርካታ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አሉ። ለአብነት ያህል ክርስቶስ ከመሞቱ ከ700 አመት በፊት የተነገረው የኢሳይያስ

ትንቢት እንዲህ ነው፦ ***‹‹እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ››*** (ኢሳይያስ 53፡5-6)። የክርስቶስ ሞት ድንገተኛ አይደለም፣ የሰውን ልጅ ለመቤዠት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ እንጂ።

ክርስቶስ ሁሉን በማወቅ ችሎታው ሊሆንበት ያለውን ሁሉ ያውቅ ነበር። በማቴዎስ 20፡17-19 እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን፦ ***‹‹ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሳለ፥ በመንገድ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ። እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፣ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥ ሊዘባበቱበትም ሊገርፉትም ሊሰቅሉትም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው››።*** ክርስቶስ ያለማንም አስገዳጅነት በፈቃዱ በእኛ ፈንታ ሊሞትንን ወሰነ።

ክርስቶስ በተዋህዶ ሰውም አምላክም ነው። ሊሆንበት ያለውን ከማወቅ ባሻገር ሥጋ እንደመልበሱ በሞቱ ተጨንቆ ነበር። ኢየሱስ ከሞቱ ቀን ቀደም ብሎ ባለው ምሽት በጌቴ ሰማኒ የአታክልት ሥፍራ በነበረበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ በሉቃስ 22፡41-44 እንዲህ እናነባለን፦ ***‹‹ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር። ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው። በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ››።*** ክርስቶስ በእርግጥ በመስቀሉ ሞጥ ነው ያዳነን።

በተጨማሪ በ1ጴጥሮስ 2፡24 ላይ የሚከተለውን እናነባለን፦ ***‹‹ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ››።*** በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነን እንድንታይ ክርስቶስ የኃጢአታችንን እዳ መክፈል ነበረበት። ሰው በዚህ መንገድ ጻድቅ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ሲታይ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የድነት መንገድ ተቀብሏልና ከዘላለም ፍርድ ይድናል።

የመስቀል ሞት የሰው ልጅ ሰውን አሰቃይቶ ለመግደል ካበጃቸው የስቃይ ፍርዶች አሰቃቂው ነው። ከዚህ የባሰ የለም። ጌታችን በዚህ መስቀል ላይ መግለጽ በሚያስቸግር ስቃይና ጣር ለስድስት ሰአታት ቆየ። እግዚአብሔር

እኛን ለማዳን ጻድቅ ይሆን ዘንድ ቅጣታችንን በመቀበል ስለእኛ ሞተ። ምን አይነት ፍቅር ነው! እርሶና እኔ ቃሉን ለመታዘዝ ክርስቶስ የከፈለው ዋጋ በቂ ምክኒያታችን አይሆንምን?

## የትምህርት 5 ጥያቄዎች

## ክርስቶስ ቅጣታችንን ተቀብሎልናል

1) (ሮሜ 5፡6-10) የጸደቅነው

ሀ) በመልካም ሥራችን ነው

ለ) ቤተክርስቲያናችን ነው

ሐ) በክርስቶስ ደም ነው

2) ክርስቶስ ለእኛ የሞተው፣ እኛን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

3) (ዮሐንስ 14፡6) ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ስንት መንገዶች አሉ?

ሀ) በራሳችን መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን

ለ) ክርስቶስ ብቸኛው መንገድ ነው

ሐ) ስመጥሩ በሆኑ ሰዎች አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን

4) እግዚአብሔርን ማገልገል ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ዋስትናችን ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

5) የክርስቶስ ሞት በእግዚአብሔር የዘላለም የድነት እቅድ ውስጥ ነበር።

ሀ) አውነት

ለ) ውሸት

6) (1ጴጥሮስ 2፡24) ክርስቶስ ሲሞት የማንን ኃጢአት ነው የተሸከመው?

ሀ) የራሱን

ለ) የእኛን

ሐ) የተወሰኑ ጻድቃን ኃጢአት ስለሌለባቸው የተቀሩትን ሰዎችን ኃጢአት ሁሉ

7) ክርስቶስ ለአለሙ ሁሉ ኃጢአት ዋጋን ስለከፈለ ሁሉም ይድናሉ።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

## ትምህርት 6

## የእግዚአብሔር ልጁን በእኛ ፈንታ የመተካት መርህ

**ሀ. የእግዚአብሔር ጸጋ፣ አዳምና ሔዋን ባለመታዘት እግዚአብሔርን በበደሉበት ወቅት ተገልጧል።**

***ዘፍጥረት 2፡15-17*** *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው ።እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ& ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን* ***ሞትን*** *ትሞታለህና።"*

***ዘፍጥረት 3፡***

***፡6-7*** *ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፣ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፣ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤* ***የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው*** *ለእነርሱ ለራሳቸው* ***ግልድም አደረጉ።***

***፡8-12*** *እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል* ***ተሸሸጉ።*** *እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ። ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ። በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤* ***ዕራቁቴንም*** *ስለ ሆንሁ* ***ፈራሁ፤*** *ተሸሸግሁም። እግዚአብሔርም አለው። ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?* ***አዳምም አለ።*** *ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና* ***በላሁ።***

***፡21-24*** *እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ* ***የቁርበትን ልብስ*** *አደረገላቸው፣* ***አለበሳቸውም...።***

አዳምና ሔዋን **አንድ** ሕግ ተሰጣቸው፤ እርሱንም አልታዘዙም። ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ሞከሩ (ይህ **የበለስ ቅጠሎች ሰፍተው በመልበሳቸው ተመስሏል።**) እርስ በእርሳቸው ተካሰሱ። ለአመጻቸውም የሚገባቸውን አገኙ፤ ይህም **ፍትህ** ይባላል። ከዚያም እግዚአብሔር የማይገባቸውን ነገር ሰጣቸው፤ ይህ ደግሞ **ፀጋ** ይባላል። ይህም እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንስሳ **በእነርሱ ፈንታ በመታረዱ** ተመስሏል። ምንም በደል የሌለበት እንስሳ በእነርሱ ኃጢያት ምክንያት ታርዷል። የዚህ እንስሳ መስዋዕት፣ ኋላ ለሚመጣውና ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጢያት ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ለሚሰጠው ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌው ነበር።

**ለ. ፋሲካ - ሌላው የክርስቶስ በእኛ ምትክ የመሆን ምሳሌ**

*ዘጸአት 12፡1 በግብፅ ምድር እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፦*

*፡12-13 እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ፣ በግብፅም አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ፤ በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ **ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ**፤ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።*

*፡21-22 ሙሴም የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠርቶ አላቸው። በየቤታችሁ ጠቦት ምረጡ፣ ወስዳችሁም **ለፋሲካ እረዱት**። ከሂሶጵ ቅጠልም ጭብጥ ውሰዱ፣ በዕቃ ውስጥ ባለውም ደም ንከሩት፣ በዕቃውም ውስጥ ካለው ደም **ሁለቱን መቃኖችና ጉበኑን እርጩ**፤ ከእናንተም አንድ ሰው ከቤቱ ደጅ እስኪነጋ ድረስ አይውጣ።*

*፡23 እግዚአብሔር ግብፃውያንን ይመታ ዘንድ ያልፋልና፤ ደሙንም በጉበኑና በሁለቱ መቃኖች ላይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በደጁ ላይ ያልፋል፣ አጥፊውም ይመታችሁ ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም*

*፡29-30 እንዲህም ሆነ፤ እኩል ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር፣ በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኵር ድረስ፣ የግብፃውያንን በግብፅ ምድር የተገኘውን በኵር ሁሉ፣ የእንስሳውንም በኵሮች ሁሉ መታ። ፈርዖንም ባሪያዎቹም ሁሉ ግብፃውያንም ሁሉ በሌሊት ተነሡ፤ የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና በግብፅ ምድር ታላቅ ልቅሶ ሆነ።*

*ዮሐ. 1፡29 በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ ፦ እነሆ **የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ**።*

*1ቆሮ. 5፡7 "ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ። **ፋሲካችን ክርስቶስ** ታርዶአልና።*

እስራኤላውያን በግብፅ **የባርነት ቀንበር** ስር ነበሩ። ጠቦት በእነርሱ **ምትክ** ተገደለ። የጠቦቱ **ደም** ባለበት ቤት ላይ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ይከለከል ነበር። ጌታ ደሙን በመቃኖቹ ላይ እና በጉበኑ ላይ ሲመለከት «**ፍርድ በዚህ ቤት ላይ አስቀድሞ ሆኗል ይላል**።$

**ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ #በእኛ ፈንታ$ መሞቱ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀው የድነት መንገድ ነው።**

*ኢሳ. 53፡4-6 በእውነት **ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል**፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን **ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ**፤ **የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን**። እኛ ሁላችን*

እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ **እግዚአብሔርም** **የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ**።

2ቆሮ. 5፡21 እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ **ኃጢአት አደረገው**።
ገላ. 3፡13 በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተፅፎአልና ክርስቶስ **ስለ** **እኛ** **እርግማን** **ሆኖ** ከህግ እርግማን ዋጀን።
1ጴጥ. 3፡18 ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ **ጻድቅ** **ሆኖ** **ስለ** **አመጸኞች** አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክኒያት ሞቶአልና፣ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፣

**መ) የዳንኩት ስለሚገባኝ ሳይሆን ከፍቅሩ የተነሳ ነው።**
ሮሜ. 4፡4-8 ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቆጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ፣ **ኃጢአተኛውንም** በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል። እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር **ያለ** **ሥራ** ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል። ዓመፃቸው **የተሰረየላቸው** ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤ ጌታ **ኃጢአቱን** **የማይቆጥርበት** ሰው ብፁዕ ነው።
ኤፌ. 1፡3-8 በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። **ዓለም** **ሳይፈጠር**፣ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ **መረጠን**። በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም **እንዲያው** የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ። በውድ ልጁም፣ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፣ በደሙ የተደረገ **ቤዛነታችንን** አገኘን እርሱም የበደላችን **ስርየት**። **ጸጋውንም** በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን።
ቲቶ 3፡3-8 እኛ ደግሞ አስቀድመን **የማናስተውል** ነበርንና፤ **የማንታዘዝ፣** **የምንስት፣** ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ **ባሪያዎች** የምንገዛ፣ በክፋትና በምቀኝነት **የምንኖር፣** የምንጣላ፣ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን። ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር **ቸርነትና** **ሰውን** **መውደዱ** በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፣ **እኛ** **ስላደረግነው** **በጽድቅ** **ስለ** **ነበረው** **ሥራ** **አይደለም**፤ ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፣ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው። ቃሉ የታመነ ነው። …

***ሠ) በ #ክርስትና$ እና በ #c¨¨< Y`®ƒ/ሐይማኖት$ መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው;***

**#ሐይማኖት$** በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖርህ **<u>አንተ</u>** **<u>ራስህ</u>** አንድ ነገር ማድረግ ትችላለህ ብሎ ሲያስተምር፣ **#ክርስትና$** ግን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖርህ የሚያደርግህ **<u>ክርስቶስ</u>** በአንተ ፈንታ ያደረገልህ የመስቀል ስራ ብቻ ነው ብሎ ያስተምራል።

*ዮሐ. 14፡6 እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም*

*ሐዋ. 4፡12 መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና*

---

**የትምህርት 6 ጥያቄዎች**

**የእግዚአብሔር ልጁን በእኛ ፈንታ የመተካት መርህ**

1) (ዮሐንስ 1፡29) የአለሙን ኃጢአት የሚያስወገደው

ሀ) የበጎች ደም

ለ) የእግዚአብሔር በግ (ኢየሱስ)

ሐ) የቅዱሳን ደም

2) (1ቆሮንቶስ 5፡7) የአዲስ ኪዳን ፋሲካችን ማን ነው?

ሀ) በግ

ለ) ኢየሱስ

ሐ) ክብረ በአል

3) በብሉይ ኪዳን በበር ላይ የተቀባው የበግ ደም እስራኤላዊያንን ከእግዚአብሔር ቁጣ እንደታደገ፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር የኢየሱስን ደም በእኛ ላይ ሲመለከት ከቁጣው ይመለሳል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

4) (ገላቲያ 3፡13) ከህግ እርግማን ይዋጀን ዘንድ ክርስቶስ ስለ እኛ ምን ሆነ?

ሀ) ንጉስ

ለ) ሊቀ ካህን

ሐ) እርግማን

5) (ኤፌሶን 1፡3-8) እግዚአብሔር እንዲያው/በነጻ ያዳነን

ሀ) የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ

ለ) መዳን የተገባን ስለሆነ

ሐ) ጽድቃችን ስላስደሰተው

6) በ (ቲቶ 3፡3-8) መሰረት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) እግዚአብሔር እንደ ምሕረቱ መጠን አዳነን

ለ) እግዚአብሔር በጸጋ አዳነን

ሐ) እኛ ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ አዳነን

7) በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖርህ የሚያደርግህ **ክርስቶስ** በአንተ ፈንታ ያደረገልህ የመስቀል ስራ ብቻ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

## ትምህርት 7

## የእግዚአብሔር ልጅ መሆን

ገላቲያ 3፡26-27 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤››***። ሁላችን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ፍላጎት ቢኖረንም ይህ ሊሳካ የሚችለው በእምነት በኩል እንደሆነ ጥቅሱ ያስረዳል። በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ነው የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የሚያደርገን።

ዮሐንስ 1፡12-13 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤››።*** ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔር ልጅነት ስልጣን የተሰጣቸው እነማን እንደሆኑና ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይነግረናል። የልጅነት ስልጣኑ የተሰጠው ክርስቶስን ለተቀበሉ ሲሆን ይህን የሚያደርጉ አማኞች ከእንግዲህ ወዲያ ፍጥረታዊ ሰዎች ብቻ እንዳልሆኑ ያበስራቸዋል።

የእግዚአብሔር ልጅና ቤተሰብ ለመሆንና ዳግም መወለድ ይኖርብናል። ጌታችን በዮሐንስ 3፡3 ላይ እንዲህ ያለ ማስጠንቀቂያ ያስተላልፍልናል፡- ***‹‹ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው››***። በመቀጠል በዮሐንስ 3፡5 ላይ እንዴት ይህ ዳግም ልደት እንደሚከናወን ያስረዳናል፡- ***‹‹ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም››።*** የክርስቶስ ደም ዳግመኛ ‹‹ከውሃና ከመንፈስ›› የተወለዱትን ሰዎች ኃጢአት ሁሉ ያነጻል።

መንግስተ ሰማይን የሚወርሱት የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ናቸው። በ1ጴጥሮስ 1፡4 እንዲህ ይላል፡- ***‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል››።*** በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጅ ሆነዋል? ይህን ካላደረጉ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት በሰማይ ርስት የሎትም።

## የትምህርት 7 ጥያቄዎች

## የእግዚአብሔር ልጅ መሆን

1) (ገላቲያ 3፡26-27) የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆነው

ሀ) በእምነት

ለ) በጥረታችን

ሐ) ከክርስቲያን ቤተሰብ በመወለድ

2) (ዮሐንስ 1፡12-13) የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን የሌላቸው እነማን ናቸው?

ሀ) ክርስቶስን የተቀበሉ

ለ) በስሙ የሚያምኑ

ሐ) ክርስቶስን የማይቀበሉ

3) መንግስተ ሰማይን ለመውረስ

ሀ) ከጥሩ ዘር መወለድ ያስፈልጋል

ለ) የተማረ መልከ መልካም ካህን መሆን ያስፈልጋል

ሐ) ‹‹ከውሃና ከመንፈስ›› ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል

4) (1ጴጥሮስ 1፡4) በሰማይ ርስት ያላቸው

ሀ) ምርጥ አገልጋዮች ናቸው

ለ) ደግ ሰዎች ናቸው

ሐ) ዳግም የተወለዱ ናቸው

## ትምህርት 8

### ለመዳን፣ የእኔ ድርሻ ምንድን ነው?

የሰው ዘር ከውድቀት በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መቅረብ ባለመቻሉ፣ ክርስቶስ ለዚህ ተስፋ ቢስ የሰው ዘር ወኪል በመሆንና በመታዘዝ ጻድቅ ሕይወቱን በሰው ልጅ ፊንታ ለእግዚአብሔር አቀረበ። የሰው ልጅ ሊሸከማት ያልቻለውን የኃጢአት ቅጣት በእርሱ ፊንታ በመሸከም የኃጢአት ስርየትን አስገኘለት። ከዚህም የተነሳ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደ ጻድቅ ተቆጠረ፤ ክርስቶስ ግን እንደ ኃጢአተኛ ተቆጠረ። ሐዋሪያው ይህን ታላቅና አስደናቂ ልውውጥ ***«እኛ በእርሱ (በክርስቶስ) ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን (ክርስቶስን) ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው›››*** በማለት ገልጦታል **(2ቆሮንቶስ 5፡21)**። በአንድ በኩል ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር እርቅና ሰላም የሚኖረው ክርስቶስ በእርሱ ስፍራ የሕግን ቅጣትና እርግማን በመሸከሙ ሲሆን **(ገላቲያ 3፡13)** በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ ጽድቅ ውስጥ በመቆሙ ነው **(1ቆሮንቶስ 1፡30-31)**።

የክርስቶስ ሞት የእኛ ምትክ መሆኑ የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር እርሱ በእኛ ምትክ መሞቱን፣ የእኛን ህማም መታመሙን፣ የእኛን በደል መሸከሙን (ኢሳይያስ 53) ነው። ኢየሱስ ስለ እኛ ቆሰለ፣ ስለ እኛ ተዋደረ የማይገባውን ያውም የመስቀል ሞት ለመሞት የታዘዘ ሆነ (ፊሊ. 2፡8)። ጤነኛ የሆነ አእምሮ ሁሉ ይህን ካነበበ በኋላ «ግን ለምን?›› ብሎ ሊጠይቅ ይገባዋል። መልሱም ሊያድነን፣ ከፈጣሪያችን ጋር ሊያስታርቀን፣ ቅዱስ ሕዝብ ሊያደርገን፣ ቀድሞ ወደ ነበርንበቱ ክብር መልሶ ሊያመጣን የሚል ይሆናል። ይህ የመዳን መንገድ ብቸኛው የመዳን መንገድ ነው (ዮሐንስ 14፡ 6)፣ ከዚህ የተሻለ የመዳን መንገድ ለመፈለግ ማሰብም ሆነ ማድረግ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጥበበኛ ነኝ ከሚል ትእቢተኛ ልብ የሚመነጭ ከመሆኑ ባሻገር የኢየሱስን ሞት ከንቱ ማድረግ ይሆናል **(ገላቲያ 2፡21)** ደሙንም ማክፋፋት ይሆናል **(ዕብራዊያን 10፡29)**።

### ኢየሱስ ይህን ሁሉ ከፈጸመልኝ የእኔ ድርሻ ምንድር ነው?

እርስዎን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ የሚቀር ሌላ መሥዋዕት እንደሌለ ይወቁ፣ የኢየሱስ መሥዋዕት ፍጹም፣ ንጹህ፣ ቅዱስ፣ በቂ በመሆኑ እርስዎን ለማዳን የሚችል እንደሆነ ይመኑ። ይህንን የማዳን መንገድ ሙሉ ለማድረግ ከእምነት ውጪ ከእርስዎ ምንም እንደማይጠበቅ ይመኑ። ከዚህ ውጪ ምንም ነገር

ለማድረግ በሚንቀሳቀሱበት ቅስበት የኢየሱስ የመስቀል ሥራ ጎዶሎና ያለእኔ እርዳታ በራሱ ሊቆም የማይችል ደካማ ሥራ ነው እያሉ እንደሆነ አይዘንጉ። «ለመዳን (ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ) ከማመን ውጪ ከኔ የሚጠበቅ እኔ የማዋጣው ነገር የለም ነው የምትለኝ)' የሚሉኝ ከሆነ፣ እኔ ደግሞ በተራዬ አንድ ጥያቄ እንድጠይቆ ይፍቀዱልኝ፦ «ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እርሶ ሊያደርጉት የሚችሉት አንዳች ነገር ቢኖር ኖሮ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለዚህ ሥቃይ አሳልፎ የሚሰጠው ይምስሎታል?

ኢየሱስ በመሥቀሉ ሥራ ሞትዎን እንደሞተልዎ ሥቃዮን እንደ ተሰቃየልዎ፣ ቢያምኑ ለነፍስዎም ቤዛ አድርጎ ሕይወቱን ስለ እርስዎ አሳልፎ እንደ ሰጠልዎ ቢያምኑ፣ እግዚአብሔር በእርስዎ ላይ የተቆጣውን ቁጣ በእርስዎ ምትክ ሆኖ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ እርቃኑ በቀራንዮ ኮረብታ ላይ በተገኘልዎ አዳኝ ላይ ማሳረፉና እርስዎም በዚህ ምክኒያት ከዚያ አስፈሪ ቁጣ ማምለጥዎን ቢያምኑ፣ ከተጣልዎ ፈጣሪ ጋር እርቅ ፈጥረዋልና በእርግጥ የዘላላም ሕይወት አለዎት!! በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ምክኒያት (እርሱን ለብሰው) ስለሚታዩ ጻድቅና ቅዱስ ለርሰቱም የሚመጥኑ ሆነው ይታያሉ።

ጸሎት መጸለይ፣ ጦም መጦም፣ ችግረኛ መርዳት፣ በቅድስና ለመኖር ራስን መግዛትና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ከአምላኩ ጋር ከተታረቀና የዘላለም ሕይወት እንዳለው ከሚያምን አማኝ ሁሉ የሚጠበቅ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እያንዳንዱ ሰው ሽልማት የሚቀበልበት መመዘኛዎች ናቸውና የሚናቁ ነገሮች አይደሉም **(ራዕ. 22፡12)**። ሆኖም ግን እነዚህ ነገሮች በአንድ ላይ ተቆልለው እንደተራራ ቢከመሩ ክርስቶስ ለእርሶ ካደረገልዎ የመስቀል ሥራ አንጻር የኢምንት መጠን እንኳ ሊቸራቸው አይችልም፤ ፈጽሞም ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅዎ አይችሉም።

---

## የትምህርት 8 ጥያቄዎች

### ለመዳን፣ የእኔ ድርሻ ምንድን ነው?

1) (2ቆሮንቶስ 5፡21) ኃጢአት ያላወቀውን ክርስቶስን ስለ እኛ ኃጢአት ያደረገው

ሀ) ተጨማሪ የራሳችንን ጽድቅ ማድረግ እንድንችል

ለ) በኃጢአት ጸንተን ለመኖር ምክኒያት እንድናገኝ

ሐ) እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንባል

2) (1ቆሮንቶስ 1፡30-31) ጽድቃችን፣ ቅድስናችንና ቤዛነታችን ማን ነው?

ሀ) መልካም ምግባራችን

ለ) ጥረቶቻችን

ሐ) ክርስቶስ ኢየሱስ

3) (ገላቲያ 2፡21) ሰው የክርስቶስን ሞት ከንቱ የሚያደርገው ምን ብሎ ሲያምን ነው?

ሀ) ጽድቅ በሕግ በኩል ነው ብሎ ሲያምን

ለ) ጽድቅ በጸጋ ነው ብሎ ሲያምን

ሐ) ጽድቅ በማመን ነው ብሎ ሲያምን

4) እኔን ለማዳን የኢየሱስ የመስቀል ሥራ ብቻውን በቂ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

5) መጸለይ፣ መጾም፣ መመጽወት፣ ወዘተ… ከዳነ ሰው የሚጠበቁ መልካም ተግባራት ናቸው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

6) (ራዕይ 22፡12) መምድር ላይ ያሳየነው መታዘዝ፣ መልካም ሥራ

ሀ) ምንም ዋጋ የላቸውም

ለ) መንግስተ ሰማይ ለመግባት ድፍረቶቻችን ናቸው

ሐ) በክርስቶስ ሥራ መንግስተ ሰማይ ስንገባ ምንዳ/ዋጋ ያሰጡናል

## ትምህርት 9

## ንስሃ

ኢየሱስ በሉቃስ 13፡3 ላይ እንዲህ ይላል፦ ***‹‹እላችኋለሁ፣ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ››***። ምርጫው ንስሃ መግባት ወይም መጥፋት ነው። ሶስተኛ አማራጭ አልቀረበልንም። ሰይጣን ግን ይህን ስናደርግ ማየት ፈጽሞ አይጥመውም። የሐዋሪያት ሥራ 17፡30 እንዲህ ይላል፦ ***‹‹እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል››።*** ሁላችን ንስሃ እንድንገባ ጥሪ ተደርጎልናል። ከምን ንስሃ እንድንገባ? መልሱ ‹ከኃጢአታችን› የሚል ነው። ***‹‹ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም››*** (1ዮሐንስ 1፡8)።

እግዚአብሔር ወደ እርሱ ፊታችንን እንድናዞር ይፈልጋል። በ2ጴጥሮስ 3፡9 ላይ እንዲ በማለት ይመክረናል፦ ***‹‹ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል››።*** ንስሃ በመግባት ከጥፋት ጥፋት እንድንድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው። በትእግስትም ይጠብቀናል። ነገ የእኛ ስላልሆነ ማንም ንስሃን ሊቀጥር አይችልም። የመዳን ቀን አሁን ነው።

ንስሃ ማዘን ብቻ አይደለም። 2ቆሮንቶስ 7፡10 እንዲህ ይላል፦ ***‹‹እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል››***። እግዚአብሔራዊ ሃዘን፣ ሃዘን ላይ አትቆምም፤ ንስሃን ትወልዳለች እንጂ። ናስሃ ስለ ኃጢአታችን ማዘን ብቻሳ አይደልም። እርግጥ ነው፣ ሰው ሳያዝን ንስሃ መግባት አይችልም። ነገር ግን ሃዘኑ ብቻውን በቂ አይደለም። ንስሃን ሙሉ የሚያደርገው የሚከተለው ነው፦ አንድ ሰው መጀመሪያ ኃጢአት መስራቱን ማወቅ አለበት፣ ከዛም በሰራው ኃጢአት ማዘን አለበት፣ በመጨረሻም ከዛ ኃጢአት ፊቱን ማዞር አለበት።

ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦ ***‹‹እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?››*** (ሮሜ 6፡1-2)። እንግዳው በእምነታችን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንንና ከፍርድ መዳናችንን የንስሃ ፍሬና በማድረግ ማሳየት ይኖርብናል። ***‹‹እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ››*** (ማቴዎስ 3፡8)።

እግዚአብሔር በልጁ በኩል መዳናችንን ፈጽሞልናል። ይህ መልካምነቱ እርሱን ደስ በማሰኘት ለመኖር በቂ ምክኒያታችን ነው። እርሱ አስቀድሞ ፍቅሩን ልጁን በመስጠትና እኛን ከዘላለም ፍርድ በማዳን ስለገለጠልን እኛም እርሱን በፍጹም ሃይላችን በፍጹም ነፍሳችንና በፍጹም ልባችን በመውደድ ትክክለኛ ምላሽ ልንሰጠው ያስፈልጋል። (1ዮሐንስ 4፡9) (ማቴዎስ 22፡37)። ይህንን ደኅንነት ችላ ካላለ ሰው ትክክለኛ ምላሽ ይጠበቃል። ይህም ምላሽ በዮሐንስ 14፡24 እና በ1ዮሐንስ 2፡4 ላይ ተገልጧል። ***‹‹የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም››*** በዮሐንስ 14፡24። ***‹‹አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም››*** 1ዮሐንስ 2፡4።

ክርስቶስን ይወዳሉ? እንግዳው ክርስቶስን የሚወዱ ከሆነ እርሱ እንዲህ ይሎታል፡- ***‹‹ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤››*** (ዮሐንስ 14፡15-16)።

---

## የትምህርት 9 ጥያቄዎች

### ንስሃ

1) (ሉቃስ 13፡3) ንስሃ የማንገባ ከሆነ

ሀ) እንጠፋለን

ለ) እግዚአብሔር ያልፈናል

ሐ) መንግስተ ሰማይ እንገባለን

2) (ሐዋሪያት ሥራ 17፡30) እግዚአብሔር ሰዎች ምን እንዲሆኑ ያዛል?

ሀ) በመረጡት መንገድ እንዲኖሩ

ለ) ንስሃ እንዲገቡ

ሐ) በኃጢአታቸው ጸንተው እንዲኖሩ

3) ሃዘን በራሱ ንስሃ ማለት ሊሆን ይችላል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

4) የዳኑ ሰዎች

ሀ) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አይፈጽሙም

ለ) እግዚአብሔርን አይወዱም

ሐ) እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይወዳሉ

# ትምህርት 10

## የመልካም ምግባራት ፋይዳ ምንድን ነው?

በመልካም ምግባራችን - ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ ማምለጥ፣ የእግዚአብሔር ልጅ መባልና ከሞት ማምለጥ እንደማንችል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን በቀደሙት ትምህርቶች ላይ ተመልክተናል። ይህ ማጠቃለያ አንድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያስገድደናል - ‹የመልካም ምግባሮቻችን ፋይዳ ምኑ ላይ ነው?› የሚል። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ በቂ ምላሽ አለው። መልካም ምግባሮቻችን የዘላለም ሕይወት የሚያስጡን ባይሆንም ዋጋ ግን አላቸው። ይህም ዋጋ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሽልማት ተብሎ ተጠቅሷል።

ለክርስቲያኖች ብቻ የተዘጋጀው ይህ የሽልማት ሥነ-ሥርዓት ፈፅሞ ከደኅንነት ጉዳይ ጋር የተገናኘ አይደለም። ይህ በመስቀሉ ላይ የተፈፀመ ጉዳይ ነው። ይህ ሽልማት እኔ ለእግዚአብሔር ካደረኩት ተግባር ጋርም አይገናኝም። እግዚአብሔር እኔ በራሴ ማድረግ የምችለውን ነገር አይፈልገውም። ይህ ሽልማት የሚያያዘው በምድር የሕይወት ዘመኔ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለኝ ሕብረት አማካኝነት በእምነት እርሱ በእኔ ሕይወት ውስጥ ፍሬ እንዲያፈራ ከፈቀድኩለት ጉዳይ ጋር ብቻ ነው። ይህንን ሰማያዊ ሽልማት ከምድራዊ ሽልማት ጋር ላነፃፅረው አልችልም። ነገር ግን ይህ ሽልማት በሰማይ ባለኝ የሕይወት ሁኔታ/quality ላይ በሆነ መልክ ተፅዕኖ አሳድራል። ሽልማት ከቅጣት ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ ክርስቲያኖች ይህንን ጉዳይ ቸል ሊሉ አይገባም። እግዚአብሔር ይህንን ጉዳይ ታላቅ ነው ካለ በእርግጥ ታላቅ ነው!

**እያንዳንዱ ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቀርባል።**

*ሮሜ. 14፤10-12 አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና። እኔ ሕያው ነኝ፣ ይላል ጌታ፣ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና። እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።*

*2ቆሮ. 5፤9-10 ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን። መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፣ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።*

*2ጢሞ. 4፤7-8 መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፣ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፣ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።*

*ራዕ. 22፤12 እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።*

**ስለ የትኞቹ ነገሮች ነው አማኞች የሚሸለሙት; ከዚህ በታች የተገለፁት፣ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲሰራ በፈቀድንለት መጠን ሊሆኑ ከምንጠብቃቸው ፍሬዎች ናሙናዎች ናቸው።**

*ምሳሌ 19፤17 ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፣ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል።*

*ማቴ. 5፤11-12 ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፣ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።*

*ማቴ. 5፤44-46 እኔ ግን እላችኋለሁ፣ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፣ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?*

*ሉቃስ 6፤35 ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፣ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል፣ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፣ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና።*

*ማቴ. 19፤27-30 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ። እነሆ፣ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? አለው። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተስ የተከተላችሁኝ፣ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፣ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ። ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል። ነገር ግን ብዙዎቹ ፊተኞች ኋለኞች፣ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።*

*ሮሜ. 8፤17-18 ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።*

*ኤፌ. 6፤5-8 ባሪያዎች ሆይ፣ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፣ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና።*

*ቆላ. 3፤22-24 ባሪያዎች ሆይ፣ በቅን ልብ ጌታን እየፈራችሁ እንጂ፣ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ሳትሆኑ፣ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፣ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና። የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና።*

*ፊሊ. 4፤1 ስለዚህ፣ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣ ደስታዬና አክሊሌ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ፣ እንዲሁ በጌታ ቁሙ፣ ወዳጆች ሆይ።*

*1ተሰ. 2፤19-20 ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና።*

*ያዕ. 1፤12 በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።*

*ራዕ. 2፤10 ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፣ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፣ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።*

እያንዳንዳችን ቢያንስ ሦስት ሐብቶች አሉን፦ ጊዜ፣ ጉልበትና ያለን ንብረት። መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ሃብቶቼን እንዲጠቀም በሕይወቴ ውስጥ ስፈቅድለት ከወርቅ፣ ብርና የከበረ ድንጋይ ዘላለማዊ ሽልማት ፍሬ ያለውን ነገር ለእኔ ይሰራል። እነዚህ ሀብቶቼን መንፈስ ቅዱስ እንዳይጠቀም እንቅፋት ስሆንበት ደግሞ ከእንጨት ከገለባና አገዳ ዘላቂነት የሌለውን ለሽልማት የማያበቃ ሕንፃ ራሴ ለራሴው እሰራለሁ (1ቆሮንቶስ 3፡10-15)።

ሽልማት፣ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ ፍሬ እንዲያፈራ ከእርሱ ጋር በሕብረት በመጣመር በእምነት የኖርኩበት ኑሮ ውጤት ነው። በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መፅሀፍ የመጨረሻ የራዕይ ክፍል ላይ እነዚህን የጌታ ቃሎች እናገኛለን። *‹‹እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ*

*ከእኔ ጋር አለ።›› (ራዕ. 22፤12)* ደኅንነት ስጦታ ቢሆንም በሕይወታችን ላሳየነው ታማኝነት ሽልማት የምናገኝበትና ታማኝ ላልሆንበት ደግሞ ሽልማት የምናጣበት ጊዜ አለ።

በእርግጥ ነው እግዚአብሔርን ከፍቅር በመነሳትና ለእርሱ ክብር ስንል ልናገለግለው ይገባል። የሽልማት ባህሪንም መረዳት እንዲሁ እንድናደርግ ያስተምረናል። እግዚአብሔር ደኅንነትን ይሰጠናል። ይህን በእምነት የምንቀበለው ነው። ደግሞም ስለ መልካም ሥራችን ይሸልመናል። እግዚአብሔር ፀጋውን እስከተጠቀምንበት ድረስ መፈለግንና ማድረግን <u>በእኛ</u> <u>ውስጥ</u> <u>ሆኖ</u> <u>ይሰራል</u> (ፊል 2፤12-13)። ነገር ግን ለማገልገል <u>መፍቀድ</u>ና ይህንንም ለማድረግ <u>ትጋት</u> ከእኛ የሚጠበቁ <u>የእኛ</u> <u>ድርሻዎችና</u> የእኛ አስተዋፅኦዎች ናቸው። እናም እግዚአብሔር ይህንን ነገራችንን፣ ሽልማት እንደሚገባው አድርጎ ይቆጥረዋል።

*1ቆሮ. 15፤10 ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፣ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።*

*ቆላ. 1፤29 ለዚህም ነገር ደግሞ፣ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፣ እደክማለሁ።*

---

**ኃጢአት ወይም አለመታዘዝ የሚያስከትሉት የአሁንና የመጪው ጊዜ ውጤቶች**

---

ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር፣ ሁሉን የኃጢአት ውጤቶች ያጠቃለለ ባይሆንም ኃጢአት በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚናቅ ተግባር አለመሆኑን በከፊል ያሳያል።

**1. ከጌታ ጋር ያለንን ሕብረት ያሳጣናል።** በአንድ ሰው ውስጥ ያለ የታወቀ ኃጢአት ከጌታ ጋር ያለን የቅርብ ግንኙነት ያውካል፤ የግለሰቡን ደስታና ሰላምን ያጠፋል (መዝ 32፤3-4)።

**2. ከጌታ የሆነ መለኮታዊ ዲሲፕሊን/ሥነ ስርዓት መማር።** <u>የሥነ</u> <u>ስርዓት</u> <u>ትምህርትን</u> <u>እንደ</u> <u>ቅጣት</u> <u>ማየት</u> <u>የለብንም።</u> ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ስነ ስርአት የማስያዝ ትምህርት፣ አብ ልጆቹን ለማሰልጠን እና ለማሳደግ የሚጠቀምበት መልካም መንገድ ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በፈተና፣ በመከራ፣ በውድቀት፣ በአስቸጋሪ ሁኔታና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ያሰለጥነናል። በግትርነታችን መቀጠል ስንፈልግ ስቃይና መከራችን እያደገ እንዲመጣ ይፈቅዳል። የዚህ ሁሉ አላማው ደግሞ እኛን ወደ እርሱ መመለስ ነው (ዕብ 12፤5-11)። አማኙ ባለመናዘዝ ፀንቶ ከኖረ እንደ አናንያ እና ሰፒራ (ሐዋ 5) እና በቆሮንቶስ እንደነበሩ አንዳንድ

ኃጢአታቸውን መናዘዝ እምቢ እንዳሉ አማኞች አካላዊ ሞትን ሊቀምስ ይችላል (1ቆሮ 11፤28 እንዲሁም 1ዮሐ 5፤16-17)።

**3. ኃይልና ፍሬያማነትን ማጣት።** *ኃጢአታችንን በእውነተኛ ልብ መናዘዝ ስናቆም በውስጣችን ያለውን መንፈስ እናጠፋለን። ይህ ማለት ደግሞ በእምነት በእግዚአብሔር አቅርቦት መኖር አቁመን በሥጋ ኃይል መኖር ጀመርን ማለት ነው። በሥጋችን ማስተዋል ሕይወትን ወደ መምራት ዘወር እንላለን* (ገላ. 3፡1-5፣ 5፡5፣ ኤር. 2፡12-13) *የዚህ ውጤቱ ደግሞ የሥጋ ፍሬና፣ ፍሬቢስ መዘዙ ይሆናል* (ገላ5፤19-21.26)። *የእምነትና የመታዘዝ ሕይወት ደግሞ በእርሱ ውስጥ ከመኖር ውጪ የማይታሰብ ነው* (ዮሐ 15፤1-7)።

**4. ከአጋጣሚዎች ጋር መተላለፍ።** *ሕይወታችንን የሚመራው ጌታ ሳይሆን ራሳችን ስንሆን ስለ ሰዎችና ስለ አገልግሎት አጋጣሚዎች ግዴለሾች እንሆናለን- ራዕይ እናጣለን። ሥጋዊ አማኞች የራሳቸውን አጀንዳዎች ከማEማEላትና የግላቸውን ግቦች ከመምታት ውጪ ሌላ ራዕይ አይኖራቸውም* (ዮሐ 4፤34)።

**5. የተሰበረ ሕብረትና ያልሰመረ ውህደት።** *ሥጋዊነት በአካባቢያችን አብረውን ከሚኖሩ ቤተሰቦቻችን፣ Õደኞቻችን፣ እና አብረውን የክርስቶስን አካል ከሚያገለግሉ አማኞች ጋር የተበላሸና ስቃይ ያለው ሕብረት እንድንገፋ ያደርገናል* (ገላ. 5፡15፣ ዕብ 12፡15)።

**6. ጤና ያሳጣል፤ ከፍተኛ ጥንካሬና ወኔን ይሰልባል።** *እርግጥ ነው ሁሉም ህመም፣ ድካምና ስቃይ የ%ጢያት ውጤት ሊሆን አይችልም፤ አይደለምም። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የኀጢአት ውጤትም ሊሆኑ ይችላሉ* (1ቆሮ. 11፡29-30፣ 1ዮሐ5፡16-17፣ ምሳሌ 17፡22፣ 14፤30)።

**7. በመጨረሻው ዘመን ሽልማት ማጣትን ያስከትላል።** 1ቆሮ 3፤13-15 *‹‹የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለ ሚገለጥ የ ቀን ያሳያልና፣ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመዎዙን ይቀበላል፤ <u>የማንም</u> <u>ሥራ</u> <u>የተቃጠለበት</u> <u>ቢሆን</u> <u>ይጎዳበታል</u>፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፣ ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል››።*

**ጥቅሶች፡-**

1ቆሮ. 3፤13-15 *‹‹የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለ ሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ እያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያለጸው ሥራ ቢጸናለት ደመዎዙን ይቀበላል፤ <u>የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል</u>፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፣ ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል››።*

1ቆሮ 4፤5 *«ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ፣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ፣ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል።´*

ከላይ የቀረበው ጥቅስ ጌታ የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ባህሪና ጥራት እንደሚመዝን በግልፅ ያሳያል። ይህንን እውነታ ከዚህ በታች ካለው ጥቅስ ጋር ያነፃፅሩ።

2ቆሮ. 5፤10 *«መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፣ እያንዳንዱ በሥጋው የተሰራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ፣ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።´*

ራዕ. 22፤12 *«እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ፣ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።´*

---

**የትምህርት 10 ጥያቄዎች**

**የመልካም ተግባርት ፋይዳ ምንድን ነው?**

1) መልካም ምግባሮቻችን የዘላለም ሕይወት ትሩፋትን ያጎናጽፉናል።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

2) ሽልማት በምድር ላይ ያለ መንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት በሰራዋቸው መልካም ተግባረት ላይ የተመሰረተ ነው።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

3) (2ቆሮንቶስ 5፤9-10) ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የምንቀርበው

ሀ) ስለ መልካም ቢሆን ወይም ስለ ክፉ ሥራችን ብድራት/ዋጋ/ደመዎዝ ለመቀበል

ለ) ስለ በጎ ሥራችን ከዘላለም ፍረድ ለመዳን

ሐ) ስለ መልካም ሥራችን መንግስተ ሰማይን ለመውረስ

4) በ (ማቴዎስ 5፤44-46) መሰረት የትኛው መልካም ሥራ ነው ዋጋ የሌለው?

ሀ) ጠላትን መውደድና የሚረግሙንን መመረቅ

ለ) ለሚጠሉን መልካም ማድረግና ስለሚያሳድዱን መጸለይ

ሐ) የሚወዱንን ብቻ መውደድ

5) (ራዕይ 22፡12) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መምድር ላይ ለሠራናት ለእያንዳንዷ መልካም ሥራ ከክርስቶስ ዋጋችንን እንቀበላለን።

ሀ) እውነት

ለ) ውሸት

6) ኃጢአት በምድር በሕይወት ሳለንና ከሞትን በሁዋላ የሚያስከትለውን መዘዝ ይጻፉ።

በምድር ላይ በሕይወት ሳለን፡- ______________________________

______________________________

ከሞትን በሁዋላ፡- ______________________________

7) በ (1ቆሮሮንቶስ 3፤13-15) መሰረት ትክክል ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ) የእያንዳንዱ ሥራ በእሳት ይፈተንና ማንም ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመዎዙን ይቀበላል።

ለ) የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፣ ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል››።

ሐ) የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱም የገሃነም እሳት ፍርድ ይቀበላል።

## ትምህርት 11

## ማጠቃለያ

### 1. የሰው ችግር በአዳም እና ሔዋን ተጀመረ

እግዚአብሔር (ሕግ) ሰጣቸው፤ እነርሱ ተላለፉት። ባለመታዘዛቸው ኃጢአትና ሞት ወደ አለም ገባ። *... ስለዚህ ምክኒያት ኃጢአት **<u>በአንድ</u>** **<u>ሰው</u>** ወደ ዓለም ገባ፣ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤...(ሮሜ 5፡12)*

*መጽሐፍ ቅዱስ* እግዚአብሔር ፍቅር፣ ፍጹም፣ ሉአላዊ፣ ቅዱስ፣ ጻዲቅ፣ ርህሩህ፣ ይቅር ባይ እንደሆነ ይናገራል። እርሱ ሊዋሽ አይችልም፣ ሊለወጥም አይችልም ። ***<u>ፈጽሞ ሊታመን የሚችል</u>*** አምላክ ነው።

ሰይጣን እግዚአብሔርን ሊታመን እነደማይችልና ለሰው ልጅችም ጥቅም የማይቆም እነደሆነ በሰው አእምሮ ውስጥ ይስላል። የሰይጣን አይነተኛ ውሸት ***<u>እኛ</u>*** ***<u>ያለ</u>*** ***<u>እግዚአብሔር</u>*** ሰላምን፣ ደስታን፣ እርካታን፣ ሃሴትንና ፍፁም ተድላን ልናገኝ እንደምንችል ማግባባት ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያቀደው ደስታ **<u>ከእርሱ</u>** **<u>ጋር</u>** **<u>ህብረት</u>** **<u>በማድረግ</u>** **<u>ብቻ</u>** የሚገኝ ደስታ ነው። (ኢየሱስ እንዲህ አለ) *... ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ **<u>ሰላሜን</u>** እሰጣችኋለሁ፣ እኔ የምሰጣችሁ **<u>አለም</u>** **<u>እንደሚሰጥ</u>** **<u>አይደለም።</u>** ዮሐ. 14፡27 ... የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅና ሰላም **<u>በመንፈስ</u>** **<u>ቅዱስም</u>** የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና። (ሮሜ 14፡17)*

### 2. መንፈሳዊ ሞት

የማያምን ሰው የሚያደርገው ነገር ሁሉ መጥፎ አይደለም። ከሰው እይታ አንፃር የማያምን ሰው በርካታ መልካም ነገሮች ያደርጋል። ችግሩ የሰው ልጅ በራሱ የሚያደርገው መልካም ነገር በእግዚአብሔር ሚዛን ፍጹም አለመሆኑ ነው። ሰው በራሱ የሚሰራው ማንኛውም ነገር እንከን ያለው፣ የተዛባ እና ክብር የጎደለው ነው። እግዚአብሔር "የእኔን ምርጥ" ነገር ሊቀበለው አይችልም።

የማያምኑ ሰዎች ተግባራቸው (ፈሬያቸው) የዘላለም ሕይወት ዋጋ የለውም፤ እግዚአብሔርንም ደስ ሊያሰኝ አይችልም። መልካም ተግባሮቻቸው ሳይቀሩ **<u>ጊዜያዊና በዚህኛው አለም ብቻ የሚቀሩ</u>** ናቸው።

*ኤፌሶን 4፡18 … **<u>ልቡናቸው ጨለማ</u>**፣ ከእግዚአብሔርም ሕይወት **<u>ራቁ</u>**፤*

*ሮሜ. 3፡23 … **<u>ሁሉ</u>** ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር **<u>ጎድሎአቸዋል</u>**፤*

*ሮሜ. 3፡10-12 … ጻድቅ የለም **<u>አንድ ስንኳ</u>** እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፣ **<u>ሁሉ</u>** ተሳስተዋል፣ **<u>በአንድነትም</u>** የማይጠቅሙ ሆነዋል…*

*ሮሜ 8፡7-8 ስለ ሥጋ ማሰብ **<u>በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና</u>**፣ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፣ **<u>መገዛትም ተስኖታል</u>**፤ በሥጋ ያሉትም **<u>እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም</u>**።*

በዚህ ጊዜ ውስጥ በነበርንበት ወቅት ከእግዚአብሔር ተለይተን የኖርን፣ በመንፈሳዊ ጭለማ ውስጥ የነበርን፣ ተስፋ ያልነበረን ሰዎች እንደነበርን ልንረዳ ይገባል።

በዚህ ወቅት አንድ ሰው ክርስቶስን ቢገፋ (ባይቀበል) እና ቢሞት ቤቱን (ሕይወቱን) በአሸዋ ላይ የሰራ ሰውን ይመስላል (ማቴዎስ 7፡24-27)። በመጨረሻም የማያምኑ ሰዎች ወደሚያገኛቸው ፍርድ ይገባል (ራዕይ 20፡11-15)። አማኞች ከዚህ ፍርድ ነፃ መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል። የዚህ አይነቱ ፍርድ የማያምኑ ሰዎችን ብቻ የሚመለከት ነው።

### 3. *የመስቀሉ ሥራ/ደኅንነት*

ይህ ጉዳይ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው። በዚህ የመስቀል ሥራ አማካኝነት በእግዚአብሔር አይን አንድ ክርስቲያን ከሞት (የእግዚአብሔር ሕይወት ከሌለበት) ወደ #ሕይወት$ (ጌታ ወደ አደረበት/ወደ ሚኖርበት ሕይወት) ተሻገረ ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከተስፋ ቢስነት ተስፋ ወደሞላው ሕይወት ተሻገረ ማለት ነው።

***ዮሐንስ 5፡24** #እውነት እውነት እላችኋለው፣ ቃሌን **የሚሰማ** የላከኝንም **የሚያምን** የዘላለም ሕይወት **አለው**፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ **ወደ ፍርድ አይመጣም**።$*

በደኅንነት ወቅት መንፈስ ቅዱስንና አዲስ ሕይወትን እቀበላለው። በደኅንነት ወቅት በክርስቶስ **<u>በተከፈለልኝ</u>** **<u>ዋጋ</u>** እና **<u>ጽድቅ</u>** የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ እችላለሁ። ይህ ሕብረት የተገኘው ከራሴ ሥራ የተነሳ አይደለም (1ቆሮ1፡30)።

### 4. ከደኅንነት በኋላስ?

<u>የእግዚአብሔር</u> <u>መሠረት</u> እና <u>የእኔ</u> <u>መሠረት</u> <u>አማራጮች</u> - እግዚአብሔር መሠረትን መስርቷል። ይህ መሠረት ደግሞ የእኔን ደኅንነት የሚወክለው ኢየሱስ ነው። ይህ እውነት ለሁሉ አማኞች በእኩል ደረጃ የሚሰራ እውነት ነው። ነገር ግን እያንዳንዳችን በዚህ መሠረት ላይ የማነፅ ምርጫ አለን። ሕንፃዎቹ በምድር ላይ በሚኖረኝ የቆይታ ጊዜ የሐብቶቼን ማለትም እንደ (ጊዜ፣ ጉልበት፣ ንብረት) አጠቃቀም የሚወክሉ ናቸው። መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋና የሕንፃ ተቋራጭ በሕይወቴ ቦታ በመስጠት እነዚህን ሐብቶቼን እንዲጠቀም ብፈቅድለት፣ እርሱ በሐብቶቼ የዘላለም ዋጋ ትርፍ ያለውን ሕንፃ ለመገንባት በእኔ ውስጥ በወርቅ፣ በብርና በከበረ ድንጋይ ያንፃል። በዚህ ሁኔታ ባልሾመው ግን ሕንፃው በእንጨት፣ በሳር ወይም በአገዳ የተገነባ ይሆናል።

**1ቆሮ. 3፡10-15** *#የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሀተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፣ ሌላውም በላዩ ያንፃል።* ***እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።*** *ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ* ***በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረም ድንጋይም በእንጨትም በሳርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ*** *የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት* ***ደመወዙን ይቀበላል*** *የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን* ***ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል*** *ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።$*

በመጨረሻም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ሞት እግዚአብሔር በአማኙ ሕይወት በተደረገው ኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣ ለመመስ ፍፁምና ሙሉ እንደሆነ ያስተምረናል። በልጁ ሙሉና ፍፁም መስዋዕት አማካኝነት እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የነበረው የፍትህ ጥያቄ በሙላት ተመልሷል። አማኙ በኃጢአቱ ምክንያት ከሚያገኘው ቅጣት በክርስቶስ የመተካት አገልግሎት አምልጧል። እዳውም በክርስቶስ ደም ተከፍሏል። አማኙ በክርስቶስ ሆኖ ለፍርድ ቀርቧል፣ ተፈርዶበታል፣ ተቀጥቷልም። <u>ቤዛነት</u> <u>ተከፍሏልና</u> እግዚአብሔር ሁለተኛ ቤዛነትትን አይጠብቅም። እግዚአብሔር አማኙን በክርስቶስ የፅድቅ ልብስ ተሸፍኖ ይመለከተዋል። ስለዚህም እግዚአብሔር በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሊከሰው የሚችለውን ነቀፋ ሊያገኝ አይችልም፤ ክርስቶስን

ለብሷልና። ስለዚህ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት አማኝ ስለ ኃጢአቱ አይቀጣም፤ ስለ ኃጢአቱም ወደፊት የሚከፍለው ዋጋ አልቀረለትም።

በዚህ ምድር ላይ አማኝ የሚያገኘው ቅጣት፣ የፍርድ ጉዳይ ሳይሆን የቤተሰብ ጉዳይ ነው። አባት ልጁን ለማረም እንደሚቀጣ እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ ለጥቅማችን ይቀጣናል/ስነ-ስርዓት አስይዘናል።